

# የቅዱስ ገብርኤል ወንድማማቾቸ ማህበር በሎስ አንጀለስ

## Saint Gabriel's Brotherhood Mahaber (Association) in Los Angeles

*"በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መልአክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና"... መዝ: 90:11*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቴያን እምነት መሰረት በኢትዮጵያውያን ዘንድ በሚወዱትና በሚያክብሩት የእግዚአብሔር መልክተኛ (መላእክ) ስም መንፈሳዊ ማህበሮችን በማቓቌአም ችግርንም ሆነ ደስታን በጋራ ለመወጣት ሲገለገሉበት ኖረዋል። የእግዚአብሔር መላክተኛ የሆነዉ ቅዱስ ገብርኤል የደስታ ምስራች አብሳሪ፡ ለአመኑት ከጭንቀትና ከመከራ አውጪ፡ የሚጠሩትን የሚሰማ ፈጥኖ ደራሽ፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም ኀያል ሊቀ መላእክ ስለሆነ እኛም በሀያልነቱና በፈጥኖ ደራሽነቱ የምናምን የኦርቶዶክስ ልጆች በቅዱስ ስሙ ሥር ተሰባስበን ፍጹም ወንድማማችነት በተሞላበት ሁኔታ መንፈሳዊና ወገናዊ አላማዎችን በጋራ ለማከናወን እንዲረዳን የቅዱስ ገብርኤል ወንማማቾቸ ማህበርን በእናታችን ወ/ሮ ድንቅነሽ ተ/ማርያም (ዚ.ዚ.) እና በጥቂት ግለሰቦች አነሳሺነት ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም አቃቁመናል::

ይህ ማህበር በሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ሥር ሆኖ ዋና ዓላማዉ:-

በሐገራችን በኢትዮጵያ በሚገኙት ቤተክርስትያናት ገዳማትና አድባራት ዉስጥ መሠረታዊ የሆኑ ቁሳቁሶችን (መገልገያቸውን) በማጣት የሰንበት ወይም የበዓላት ቅዳሴና መንፈሳዊ ትምህርት ባለማግኘት በሮቻቸዉን እንዲዘጉ የተገደዱትንና የታጎሉትን በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ መርዳትና የወንጌል ስርጭት ለሁሉ እንዲዳረስ ሙሉ ድጋፍ መስጠት ነው::

ከላይ ከተጠቀሰዉ ዋና የማህበሩ ዓላማ በተጨማሪ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባሮችም ያጠቃልላል:

ለመንፈሳዊ አገልግሎት በአርአያነትና በግንባር ቀደምትነት በመገኘት ከሌሎች መንፈሳዊ ማህበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ቤተ ክርስቲያናችንን በተመለከተ በጋራ የሚከናወኑ አገልግሎቶችን ለመፈጸምና ለድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በገንዘብም ሆነ በጉልበት እርዳታና ድጋፍ መስጠት፤

በአገራችን በኢትዮጵያም ሆነ ወይም እዚሁ በምንኖርበት አካባቢ በጊዜዉ የሚከሰቱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቀነስና ለወገናችን ፈጥኖ ደራሽ ለመሆን የምንችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር፣

በአንድ የማህበሩ አባል ላይ ሐዘንም ሆነ ደስታ ሲደርስ በግንባር ቀደምትነት በመገኘት መረዳዳትና መተሳሰብን ለማከናወን፣

ፍጹም ወንድማማችነት በተመላበት ሁኔታ በየወሩ ጸበል ጻዲቅ (ዳቦ፤ሻይ፤ ቡናና ዉሃ) በማቅረብ ቅዱስ ገብርኤል በዋለበት በሚቀርበው እሁድ እየተገናኘን ከማናቸውም አይነት ፖለቲካ ነፃ የሆነ መንፈሳዊና ማህበራዊ ውይይቶችን ማድረግ ነዉ::